ፍልሰታ

mekrez.blogspot.com/2014/08/blog-post.html

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.)፦ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !!!

ተዋዳጆች ሆይ! ዛሬ የምንማማረው በእንተ ፍልሰታ ስማርያም አይደለም። ስለራሳችን ፍልሰታ እንጂ። ኩላችንም ስለ አመቤታችን ፍልሰታ የመናገር ችገር የለብንም። ዛሬ እንድንማማርና እንድንወቃቀስ የፈለግኩት በሕይወታችን ከግብርናተዴያብሉስ ወደ ከርስቶስ ሳንፈልስ (ሳንሻገር) የአመቤታችንን ፍልሰታ ብቻ ለምናከብር ሰየኔ ቢጤዎች ነው።

እስኪ ከኩሉም አስቀድመን ለራሳችን ይኸን ጥያቄ እንጠይቀው።"በሕይወት ዘመኔ ስንት የፍልሰታ አፅዋማት አሰፋ? እነስ በዚኩ ጉዳይ ስንት ጊዜ ተናገርኩ? ለስዚኩ በዓል ለማወቅ መጓጓቴ ለማያውቁትም የማውቀውን ያኽል መናገሬ ከፋት ባይኖረውም እኔ ራሴስ ምን ለውጥ አመጣኩ? ምን ፍሬ አፈራኩ? ለስ ፍልሰታ እየተናገርኩ እኔ ራሴ ሳልፈልስ ስንት ዘመናት አሰፋ? ከአገልግሎቴ ምን ረብሕ አገኛኩ?"

ተወዳጆች ሆይ! እውነት ነው ምንም ሳንለወጥ ብዙ ዘመናትን አሳልፈናል። እኛ በሕይወት ሳንሻገር ብዙ የመሻገር (የፋሲካ) በዓላትን አከብረናል። እኛ ሳንነሣ ብዙ የመነሣት (የትንሣኤ) በዓላትን አከብረናል። እኛ በሕይወት ሳንፈልስ ብዙ የፍልሰታ በዓላትን አከብረናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለእንደዚኩ ዓይነት ምልልሳችን እንዲኽ ነው የሚለን፦"ቀንንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችኁ። ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜለሁ ብዬ እፈራችኁለኹ"/ገላ.፬ ፡፲-፲፩/። በዓላትን የምናከብራቸው ቀናትን፣ ወራትን፣ ወይም ዘመናትን ለማክበር አይደለም። እነዚኽን በዓላት ምክንያት አድርገን ራሳችንን የበለጠ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ነው። እነዚኽን በዓላት ምክንያት አድርገን የእግዚአብሔር ቸርነቱን ለእኛም ያለውን ፍቅሩን ተረድተን እንድናመሰግነው ነው። ፍልሰታ ለማርያምን የምናከብረው በእመቤታችን ላይ የምንጨምረው ነገር ስላለ አይደለም። ፍልሰታን የምናከብረው እንደ እመቤታችን እንኳን ባይኾን የዓቅማችንን ያኽል በዚኽ ጊዜአዊ መቆያችን እስካለን ድረስ በንጽሕና በቅድስና ከምንም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን በፊደላት ላይኾን በሕይወታችን ዐውቀነው አጣጥመነው የምንኖር ከኾነ ትንሣኤ፤ ፍልሰት እንዳለን እንድናውቅ ነው።

ይኽን ግምትውስጥ ባለስገባ መንገድ የምናከብረው ከኾነ ግን የእስከ አኩኑ ምልልሳችን አይሁዳዊ ምልልስ ነበር ማለት ነው። እንዴት? አይሁዳውያን ሕገ ኦሪትን የተሰጠቻቸው ጎጢአታቸውን በር ሲ መስታወትነት ዐይተው ንስሐ እንዲገቡባት ስትሰጣቸው፥ እነርሱ ግን የንስሐ ፍሬ ሳያፈሩባት እንዲኹ ለስተመኩባት ለሕይወት የተሰጠቻቸው ሕግ ሞት ኾና አግኝቷታልና። እኛም እንዲኽ ለኾነ ያይደለ ለጽድቅ የተሰጠችን ወንጌል ፍሬ የማናፈራበት ከኾነ ከርስቶስን ከማያውቁ አይሁዳውያን የባለን ነን።

አስኪ አንድ ምሳሌ አንሥተን አንማማር ፡፡ አንድ የአገር ኪስ ከሰብ በየጊዜው ተጋጣሚውን አንደምን ማሸነፍ አንዳሰበት ልምምድ የሚያደርግ ከኾነ ከሳሉቱ ይዳብራል ፡፡ተጋጣሚውንም በቀሳሱ ማሸነፍ ይቻሏል ፡፡ በአውሮፓ ታሳሳቅ ሲጎች የሚጫወቱ ከሰቦች በየአገሩ አየዞሩ አቂማቸውን አየሰኩ ያሉት በቀጣዩ ዓመት ሰዋንጪ የሚያበቃቸውን ውቤት ሰማምጣት አንጂ ተጨዋቾቹ ዕረፍት ማድረግ ስሳልፈሰጉ አይደሰም ፡፡ አኛስ! ፍልሰታን የምናከብረው ሰምንድነው? አንደ እመቤታችን መነሣት አንዳሰ አንድናውቅ ያንንም ሕይወት ገንዘብ ወይስ አንዴኩ ልማድ ስለኾነብን? ሰምንድነው የምንጦመው? ይኽ ጥያቄ አችን ወደ ቀጣዩ መፍትሔ ያመራናል!!!

ክርስትና ጠቅላላ ዕውቀት አይደለም፤ አኖ በክርስቶስ ክርስቶስም በአኖ ኾኖ አግዚአብሔርን ማምለክ ነው አንጂ፡፡

እግዚአብሔርን ማምለክ ሲባልም በንግሥ በዓሳት ሳይ መሳተፍ ፣ መዝሙር ወይም ማሳሌት ወይም ሰዓታት ሳይ መሳተፍ ፣ መጸለይ ፣ መጦም ፣ አስራት በኵራትን ማውጣት አይደለም ፡፡ እነዚኽ ኩሉ ከእውነተኛ አምልኮአችን በኋላ የሚከተሉ ናቸው ፡፡ ስለዚኽ እውነተኛ አምልኮ ከዚኽ የሚያልፍ (ከፍ የሚል) ነው ፡፡እውነተኛ አምልኮ አግዚአብሔር አኖን ምን ያኽል እንደሚያፈቅረን ማወቅ ነው፡፡

አዳም በኤደን ገነትውስጥ ሳለ እግዚአብሔርን ያውቀውነበር ፤ መፍቀሬ ሰብእ አንደኾነ ፡፡ በበደለ ጊዜ ግን ዓይነ ልቡናውታወረ ፡፡ እግዚአብሔር ስለ ፍቅሩ አዳምን ሲፈልገውሲሸሽ የነበረውም በዚኩ ምክንያት ነው ፡፡ድምጹን እንኳን መስማት የተሳነው የእግዚአብሔርን ፍቅር አልረዳብሎ ነው /ዘፍ.፫ ፡፮/ ፡፡ እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ ፍቅር ነውና ሰዎች ፍቅሩን እንረዳለት ዘንድ ይሻል ፡፡መጽሐፍ ቅዱሳችንን በሙሉ ስናነብ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ምን ያኽል የሰውፍቅርን እንደተጠማ ነው ፡፡ እግዚአብሔር አንድ አብርሃምን ሲፈልግ የነበረው ፣ በቤቱውስጥ ገብቶ ማዕድን ሲበላ የነበረው ፣ ከነ ይሥሐቅ ጋር የተወዳጀው ፣ ከእነ ያዕቆብ ጋር ሲታገል ያደረው ፣ ከእነ ሙሴ ጋር በሲና ተራራ ፵ ቀንና ሌሊት ሲጨዋወት የነበረውፍቅሩን የሚረዳለትና የሚያውቅለትን ሰውፍለጋ ነው ፡፡

እስራኤላውያን ፍቅሩን ይረዱለት ዘንድ ሕጉን በሙሴ በኩል ሰጣቸው ፡፡ ሕጉም ገና ሲዝምር ፦“እነ ውእቱ እግዚአብሔር ዘአውፃእኩከ እምድረ ግብጽ እምቤተ ቅን የት - ጽኑ አገዛዝ ከምትገዛበት ከግብጽ አገር ያወጣኩሳ ፈጥረ የምገዛሳ እግዚአብሔር እኔ ነኝ” ነው የሚሰው /ዘጸ.20 ፡2/ ፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ የሚሻው ተቀዳሚ ነገር ርሱን እንድናውቀው ነው ማለት ነው ፡፡ ስናውቀው ፍቅሩን እንረዳለታለን ፤ ደግሞም እንወዲለን ፡፡ በነቢዩ ሆሴዕ አድሮ የተናገረውም ቢኾን ፦“ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ አግዚአብሔርን ማወቅ አወድዳለኩና” ነው የሚሰው /ሆሴ.፮ ፡፮/ ፡፡ አስቀድመን እንደተናገርን ከመስገዳችን በፊት ፣ ከመጦማችን በፊት ፣ ከመጸለያችን በፊት ፣ ሰዓታት ከመቆማችን በፊት ፣ ሱባዔ ከመግባታችን በፊት አግዚአብሔር እንድናውቀው ይፈልጋል ፡፡

ከብር ይግባውና ጌታችን ና መድኃኒታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ወደዚኽ ምድር የመጣውም ሰሌሳ ዓሳማ አይደለም ፤ የሰውፍቅር ጠምቶት እንጂ /ዮሐ.፮ ፡፮/ ፡፡ ጌታችን ከጎቤአት በቀር የእኛን ባሕርይ የተዋሐደው እኛ ከርሱ ጋራ እንድንዋሐድ ነው ፡፡ የሰውነቱ ሕዋሳት ሲያደርገንም የአብፍቅሩ እንደምን ጥልቅ እንደኾነች እንድንረዳ ነው ፡፡ አብ እንድያልጎን አስኪሰጠን ድረስ እንደወደደን እንድናውቅ ነው ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኃምሳ የተሰጠን ፍቅሩን ተረድተን ለት በፍቅሩ ኖረን በእውነትወዳጃችን እንደኾነ ዐውቀን በሕይወት

እንድንኖርስት ነው።ልጅነትን አግኝተን በወይን ከርስቶስውስጥ ቅርንጫፍ
የኾንነውየወልድን የባሕርይ ልጅነት በጸጋ ተካፋይ እንድንኾን ነው።አባ
አባትብሰን እንጠራውዘንድ የልጅነትን ሥልጣን የሰጠን ስለዚኩ ነው።በዚኽም
ማንም ፍጥረትሲደርስበት የማይጭል የአባትነትፍቅሩን እንድንረዳ ነው።
በቅዱስ ቁርባን ከርስቶስ በእኛ እኛም በከርስቶስ ነውየምንኾነው።ከዚኽም
የተነሣአብን እናውቃለን።ምክንያቱም ከወልድ በቀርአብን የሚያውቀው
ስለሌለ /ማቴ.፲፩፡፳፯/ ወልድ ደግሞ በሰበሰውሥጋ ከእኛ ጋራ ስለተዛመደና
እኛም ከርሱ ጋራ ስለተዛመድን በርሱ በኩል እግዚአብሔርአብን እናውቃለን።
ገና ስንዘምርእውነተኛ አምልኮ ያለውነውም በዚኩተፈጻሚነቱን ያገኛል።
የሰውልጆች አጥተነውየነበረውእውነተኛ ሥርዓተ አምልኮታችን በከርስቶስ
(በቅዱስ ቁርባን) በኩል ተመልሶልናል።አስቀድመን እንደተናገርን ቀዳማዊ
አዳም እግዚአብሔርን ከማወቅ ርቆ መታዘዝን እምቢ ብሎ ነበር።ከርስቶስ ግን
ለአባቱ በመታዘዝ እውነተኛ አምልኮአችንን መልሶልናል።
ርግጥ ነው በቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን እናውቃለን።በቅዱስ ቁርባን
ግን በልጁ ደም ከርሱ ጋር እንታረቃለን፤ ርሱ በእኛ እኛም በርሱ እንኾናለንና
ከየትኛውም መንገድ በላይ እናውቃለን።የኤማሁስ መንገደኞችን
እናስታውሳቸው! የኤማሁስ መንገደኞች ጌታችን ከሙሴ እስከ ነቢያት ያሉ
መጻሕፍትን ሲነግራቸውልባቸውይቃጠልባቸው ነበር።ከነርሱ ጋር አራት በበላ
ጊዜ ግን ዓይናቸውተከፈተ፤ ከርስቶስንም ዐወቁት /ሉቃ.፳፬፡፴፪/።
ታድያ እኛ እግዚአብሔርን በእውነት እያመለክነው ነውወይ? በሌላ አገላለጥ
ከርስቶስ በእኛ እኛም በከርስቶስውስጥ አለን ወይ? አብን ማወቅ የምንጥለው
የከርስቶስ ሕዋሳት የኾንን እንደኮነ ብቻ ነው፤ ወልድን የምናውቀውብልቶቹ
እንደኾንን ብቻ ነው፤ መንፈስ ቅዱስንም እንደዚኩ።ታድያ እግዚአብሔርን
የምናወቀው በፊደላት ነው÷ ወይስ በእውነት በከርስቶስውስጥ ኾነን ማለትም
ቅዱስ ሥጋውን ና ከቡር ደሙን በመቀበል? በዚኽ ፍልሰታ ምን አስበናል አኹንም
እንደ አምና እንዲኩ በዘልማድ ስማከበር? እንዲኽስ ከቶ አይኩን!!! እስኪ
ከን ስሐ አባቶቻችን ጋር እንማከርና ፍልሰታን በእውነት ፍልሰታ ስማር ያም ብቻ
ሳይኾን ለእኛም እናድርገው።ይኽን እንድናደርግ የእግዚአብሔር ቸርነት
የአመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን መላዕክትተራዳኢነት ይርዳን አሜን!!!